# የኢትዮጵያ ትምህርትና ስልጠና ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ጥናት

## ለሕዝብ የውይይት መድረክ የቀረበ

## ታህሳስ 2011 ዓ.ም.

# ይዘት

- የጥናቱ ዘዴ
- እስካሁን ያሳካናቸው የትምህርትና ሥልጠና ጉዳዮች
- የትምህርትና ሥልጠና ችግሮችና ተግዳሮቶች
- አጠቃላይ ትምህርት
- ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና
- ከፍተኛ ትምህርት
- የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ፣ አመራርና አስተዳደር
- ማጠቃለያ

# ክፍል አንድ

# የጥናቱ ዘዴ

# የቅድመ ዝግጅት ምእራፍ

## አደረጃጀት፤

1.ስትሪንግ ካውንስል/Steering Council/፣

2 አስተባባሪ ቡድን/የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል/፣

3. የባለሙያዎች ኮሚቴ /Technical Committee/፤

(6 ቡድኖች 36 ባለሙያዎች ጥናቱን እንዲያጠኑ ተደርጓል።)

# የቅድመ ዝግጅት ምእራፍ ......

ስድስት መሪ ጭብጦች ፤

1. ቅድመ መደበኛና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት /ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፣
2. የሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ ትምህርት ፣
3. የመምህራን ትምህርትና ስልጠና ፣
4. ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፣
5. ከፍተኛ ትምህርትና ፣
6. የትምህርት ፖሊሲ፣ አመራርና አደረጃጀት።

# የፕሮጀክት ትግበራ ምእራፍ

## የመረጃ ምንጮች፤

ስድስት የጉድኝት መረጃ መሰብሰቢያ ቦታዎች፤

1. ፌደራል፣
2. አዲስ አበባና ደቡብ ህዝቦች ፣
3. ኦሮሚያና ጋምቤላ፣
4. አማራና ቤንሻንጉል ጉምዝ፣
5. ትግራይና አፋር፣
6. ድሬደዋ ሀረሪና ሶማሌ።

# የፕሮጀክት ትግበራ ምእራፍ

## ፌደራል

1. ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት፣
2. የፓርላማ ተወካይ፣
3. የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ተቋም አመራር፣
4. የልማት አጋሮች፣
5. የሞያ ማህበራት ፣
6. የሲቪል ሶሳይቲ ና ፣
7. የዩኒቨርሲቲ አመራር (የግልና የመንግስት )፡፡

# የፕሮጀክት ትግበራ ምእራፍ

## ክልል

1. የክልላዊ መንግስት ፕሬዘዳንት /ምክትል/፣
2. የከተማ መስተዳደር ከንቲባ /ምክትል/፣
3. የትምህርት ቢሮ ኃላፊ/ምክትል፣የትምህርት ቢሮ ኤክስፐርቶች /፣
4. አግባብነት ያላቸው የሴክተር ቢሮ ኃላፊዎች፣
5. የዩኒቨርሲቲ ፕሬዘዳንቶች ፣ የበላይ ኃላፊዎች ፣የስርዓተ ፆታ ኃላፊዎችና የተማሪ ዲኖች ፣መምህራንና ተማሪዎች ፣
6. የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅና የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ኮሌጅ ዲኖችና ዳይሬክተሮች፣
7. የዞንና የወረዳ የትምህርት ቢሮ ኃላፊዎች ፣
8. የአንደኛ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ ርዕሳነ መምህራን፣መምህራን፣ ተማሪዎችና ወላጆችና
9. የቅድመ መደበኛ መምህራንና ወላጆች ።

ማዕከል - ከተማ ቀመስ - ገጠር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ጥናት

# የፕሮጀክት ትግበራ ምእራፍ



ለመስክ ጥናት የተሰማሩ ባለሙያዎች፤

ሀ. ተመራማሪዎች ፣ {36}

ለ .ተባባሪ ተመራማሪዎች ፣ {73}

ሐ.የትምህርት ቢሮ አስተባባሪዎች ፣ {11}

ጠቅላላ= 110

# የፕሮጀክት ትግበራ ምእራፍ ክፍል 2 (የቀጠለ)

| ተ.ቁ | የመረጃ መሳሪያ | ጠቅላላ |
|---|---|---|
| ሀ. | የፅሁፍ መጠይቅ፣ | 11,640 |
| ለ. | የቃለ መጠይቅ፣ | 199 |
| ሐ | የቡድን ውይይት፣ | 1,023 |
| ጠቅላላ ድምር = | | 12,862 |

# ዓለም አቀፍ ትምህርታዊ ጉብኝት ምዕራፍ
# መስከረም 27-ጥቅምት 12/2010

ዓለም አቀፍ ትምህርታዊ ጉብኝት ምዕራፍ
መስከረም 27-ጥቅምት 12/2010

**ቬትናም እና ማሌዢያ ፤**

- አጥኚ ቡድኑ ትምህርታዊ ሪፖርቱን በስድስት መሪ ጭብጦች በማደራጀት ረቂቅ የጥናት ሪፖርት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ አስረክቧል ፣
- በረቂቅ ጥናቱም ለትምህርት ሚኒስቴር የበላይ አመራር ገለጻ ተድርጓል።

# ከኤክስፐርቶች ጋር በስድስት መሪ ጭብጦች ላይ ጎን ለጎን የተደረጉ አውደጥናቶች

ከመንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ተወክለው ከመጡ ኤክስፐርቶች ጋር የተደረጉ አውደጥናቶች ፤

- ፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር፣
- አዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ፣
- ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮና፣
- የልማት አጋሮች ።

# እስካሁን ያሳካናቸው የትምህርትና ሥልጠና ጉዳዮች

# ከሃያ አራት አመት በፊት፤

- 4 ሺህ በሚሆኑ የመጀመሪያ ደረጃና 278 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በአጠቃላይ ከ2 ሚሊዩን ያልበለጡ ተማሪዎች ብቻ ይማሩ ነበር፡፡

# በአሁኑ ወቅት

- የትምህርት ተቋማት ቁጥር ከ39 ሺህ በላይ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶችና 3,300 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከ28 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን ማስተናገድ ተችሏል፡፡
- በጥቂት የከተማ አካባቢዎች ተወስኖ የነበሩት 16 ያህል ቴክኒክና ሙያ ተቋማትን ዛሬ መንግሥታችን በወሰደው ቁርጠኛ እርምጃ 1546 ተቋማት ማድረስ ተችሏል፡፡
- ሁለት የነበሩትን የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ወደ 46 ማሳደግ ችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ወደ 130 የሚደርሱ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሥራ ላይ ናቸው፡፡

## የቀጠለ...

ምንም እንኳን ባለፉት ሃያ አራት አመታት የትምህርትና ሥልጠና ውጤቶችን ያስመዘገብን ቢሆንም፤

- በፖሊሲው መሠረት ባለመፈፀም፣
- በየደረጃው በፖሊሲው ላይ ግልጽነት ባለመፍጠራችንና በአግባቡ መተግበር ባለመቻላችን
- እስካሁን ያልፈታናቸው

የትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሐዊነት፣ ጥራትና አግባብነት ችግሮቹ አገሪቱ የምትፈልገውን ብቁና በቂ የሰው ኃይል በማፍራት በኩል አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደሩ ይገኛሉ፡፡

በመሆኑም እነዚህን ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት ይቻል ዘንድ የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እየተሠራ ይገኛል፡፡

ለፍኖተ-ካርታው ግብአት የሚሆን ጥናት እንዲጠና ተደርጓል፡፡

- ችግሮችና ተግዳሮቶች አሉ፡፡

# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን

# አጠቃላይ ትምህርት







# ቅድመ መደበኛ

# ትኩረት የተነፈገውና በአግባቡም ያልተተገበረ የቅድመ መደበኛ ትምህርት

- የቅድመ መደበኛ ኘሮግራም አፈጻጸም እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ፣
- በክልሎች መካከል ያለው የአፈጻጸም ልዩነት እጅግ የከፋና ፍትሐዊነቱ በጣም የሰፋ መሆኑ፣
- ደረጃውን በጠበቀ ሥርዓተ-ትምህርት፣ መምህራንና ተቋማት ያልተመራ መሆኑ፣
- ከአለም አቀፍ (ዩኒስኮ ስታንዳርድ) እና ከሰሃራ በታች ካሉ አገሮች አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፣
- በየደረጃው ያለው አመራርም የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ በእውቀትና በቅንጅት መምራት አለመቻሉ፣

# ትኩረት የተነፈገውና በአግባቡም ያልተተገበረ የቅድመ መደበኛ ትምህርት፡

ከ2005-2009 ዓ.ም የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሣትፎ በ%



| | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 |
|---|---|---|---|---|---|
| ሴት | 25.5 | 33 | 38 | 43.1 | 44.5 |
| ወንድ | 26.6 | 34.9 | 40 | 45.8 | 47.1 |
| ድምር | 26.1 | 34 | 39 | 44.4 | 45.9 |

ሴት ወንድ ድምር

ከ2006-2009 ዓ.ም የቅድመ መደበኛ ትምህርት የጥቅል ተሳትፎ እድገት ጭማሬ በ%



## <u>እጅግ  የከፋና ፍትሐዊነቱ  በጣም የሰፋ በክልሎች መካከል የአፈጻጸም ልዩነት፣</u>

# የ2009 ዓ.ም የክልሎች የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሣትፎ በ%




| | ትግራይ | አፋር | አማራ | አሮሚያ | ኢትዮ-ሶማሌ | ቤንሻንጉል-ጉሙዝ | ደቡብ | ጋምቤላ | ሐረሪ | አዲስ አበባ | ድሬዳዋ | አገር አቀፍ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ድምር | 93.2 | 11.7 | 45.1 | 31.9 | 7.4 | 40.1 | 72.2 | 25.9 | 90.2 | 92.4 | 53.8 | 45.9 |
| ሴት | 92.9 | 11.7 | 44.6 | 30.5 | 7 | 37.8 | 69.6 | 25 | 88.4 | 91.4 | 53.2 | 44.5 |
| ወንድ | 93.5 | 11.8 | 45.6 | 33.3 | 7.8 | 42.4 | 74.9 | 26.8 | 91.9 | 93.4 | 54.5 | 47.1 |

# ከአለም አቀፍ (ዩኒስኮ ስታንዳርድ) እና ከሰሃራ በታች ካሉ አገሮች በጣም ዝቅተኛ የቅድመ መደበኛ ኘሮግራም አፈጻጸም፣



# የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት







# የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት (1ኛ - 8ኛ ክፍል) ፕሮግራም

- ፍትሐዊነትን ሙሉ በሙሉ ያላረጋገጠ ኘሮግራም መሆኑ፣
- አሁንም ቢሆን ከትምህርት ገበታ ውጪ ያሉ ሕጻናት መኖር፣
- በአንዳንድ ክልሎች የተሣትፎው ሁኔታ ወደ ኋላ የመመለስ አደጋ መኖር፣
- ከፍትሐዊነት አኳያ አሁንም ክፍቱ፣
  - በአካባቢ /በአርብቶ አደር፣ ነባር ብሔረሰቦች/
  - በጾታ መካከል፣
  - እጅግ በጣም ዝቅተኛ ተሣትፎና ተገቢውን ምላሽ ያልተሰጠው ልዩ ፍላጐት ያላቸው ሕጻናት፣
- ከብቃት አኳያ መጠነ ማቋረጡ እጅግ ከፍተኛና አደጋ መሆኑ፣

# ፍትሐዊነትን ሙሉ በሙሉ ያላረጋገጠ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት፣

## የተሣትፎ መጠኑ ከአመት አመት መዋዥቅ የሚታይበት ነው።

ከ2006-2009 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ (1ኛ-8ኛ ክፍል) የተሳትፎ እድገት ጭማሬ በ%



# ከብቃት አኳያ መጠነ ማቋረጡ እጅግ ከፍተኛና አደጋ መሆኑ፣

ከ2005-2009 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሣይክል (5ኛ-8ኛ ክፍል) ጥቅል ተሣትፎ በ%




| | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 |
|---|---|---|---|---|---|
| ሴት | 62.2 | 63.4 | 64.8 | 68.9 | 71.4 |
| ወንድ | 63.4 | 64.7 | 67.8 | 73.3 | 77.3 |
| ድምር | 62.8 | 64.1 | 66.3 | 71.1 | 74.4 |

## አሁንም ገና ወደ ት/ቤት ያልመጡ ሕጻናት አሉ

በዩኒስኮ ሪፖርት መሠረት እ.ኤ.አ በ2015 በአለም ላይ ወደ 264 ሚሊዮን የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማግኘት የሚገባቸው ሕጻናትና ወጣቶች ከትምህርት ቤት ውጪ ነበሩ።

- በ2015 በአለም ላይ እድሜያቸው ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ደርሶ ወደ ትምህርት ቤት በመምጣት መማር ሲገባቸው ከትምህርት ቤት ውጪ የሆኑ ሕጻናት፤ አንድ ስስተኛውን ቁጥር የያዙት፤ ናይጀሪያ፣ ፓኪስታን፣ ሕንድ፣ ሱዳን፣ ኢንዶነዢያና ኢትዮጵያ ናቸው።
- በተለይ ልዩ ፍላጎት ያላቸው፣ የነባር ብሔረሰቦች፣ በገጠር የሚገኙና የሴት ሕጻናት ወደ ትምህርት ቤት አለመምጣት ችግር የከፋ ነው።

# የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት





# በጣም አዝጋሚ እድገት እያሳየ ያለ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት /9ኛ ክፍል - 10ኛ ክፍል/ ፕሮግራም

## ከ2005-2009 ዓ.ም የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-10ኛ ክፍል) ጥቅል ተሣትፎ በ%

ግራፍ 8፡ ከ2005-2009 ዓ.ም የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-10ኛ ክፍል) ጥቅል ተሣትፎ በ%




ግራፍ 9፡ ከ2006-2009 ዓ.ም የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-10ኛ ክፍል) ጥቅል ተሣትፎ እድገት ጭማሬ በ%




| | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 |
|---|---|---|---|---|---|
| ሴት | | 1.1 | 0.4 | 5 | 1.8 |
| ወንድ | | 0.5 | 0.9 | 4.9 | 2.7 |
| ድምር | | 0.9 | 0.5 | 5.2 | 2.1 |

# የ2009 ዓ.ም. የክልሎች የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-10ኛ ክፍል) ጥቅል ተሣትፎ በ%




| | ትግራይ | አፋር | አማራ | ኦሮሚያ | ኢትዮ-ሶማሌ | ደቡብ | ቤንሻንጉል-ጉሙዝ | ጋምቤላ | ሐረሪ | አዲስ አበባ | ድሬዳዋ | አገር አቀፍ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወንድ | 71.4 | 18.3 | 50.3 | 41.3 | 17.3 | 58.8 | 61.2 | 114.8 | 57.9 | 107.7 | 55.4 | 48.9 |
| ሴት | 76.1 | 12.9 | 56.4 | 33.6 | 11.4 | 47.8 | 46.4 | 96.0 | 51.4 | 122.9 | 47.3 | 45.2 |
| ድምር | 73.7 | 15.9 | 53.3 | 37.5 | 14.7 | 53.4 | 53.9 | 105.9 | 54.7 | 115.6 | 51.3 | 47.1 |

# በ2009 ዓ.ም. ከ1ኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል የተማሪዎችን ብዛት የሚያሳይ



# የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርት





# ከአለም አገሮች በጣም ዝቅተኛ ተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርት ተሣትፎ፣

ማንበብ፣ መፃፍና ማስላት የሚችሉ ጐልማሶች የተሣትፎ መጠናችን ከሌሎች አገሮችና ከአለም አማካይ ጋር ሲነፃፀር



# ዋና ዋና ችግሮች

ፕሮግራሙን ለመምራት በየደረጃው የተቋቋሙት የቦርድና የቴክኒክ ኮሚቴዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ አለመግባት፤

መርሀግብሩን ለትምህርቱ ሴክተር ብቻ መተው ፣

ተገቢው አደረጃጀት የሌለው መሆኑ፣

ሥልጠናው ከጐልማሳው ሕይወት ማለትም ግብርና፣ ጤና፣ የሕይወት ክህሎት፣ ወዘተ. ጋር የተቆራኘ አለመሆን፣

ማንበብና መጻፍ ላይ ማተኮር፣

ተአማኒና ወቅታዊ መረጃ አለመኖር፣

ለፕሮግራሙ ግብአቶች (አመቻአችና ባለሙያዎች) አለመሟላት ወዘተ፣

# ብቃትና ጥራት

# እጅግ አሳሳቢ የሆነ ብክነት የሚታይበት የትምህርት ውስጣዊ ብቃት

የመጀመሪያ ደረጃ የማጠናቀቂያ ምጣኔአችን ከሌሎች አገሮችና ከአለም አማካይ ጋር ሲነፃፀር



# በፖሊሲው ላይ የተቀመጠውን ያለሳካ የተማሪዎች የመማር ውጤት

## የ4ኛ ክፍል የትምህርት ቅበላ ጥናት ውጤቶች /50% እና በላይ ውጤት ያመጡ/



# የ8ኛ ክፍል የትምህርት ቅበላ ጥናት ውጤቶች /50% እና በላይ ውጤት ያመጡ/



# የ10ኛ ና የ12ኛ ክፍል የትምህርት ቅበላ ጥናት ውጤቶች /ከ 50% በላይ ውጤት ያመጡ/



## ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ምላሽ የማይሰጥና መስተካከል ያለበት ሥርዓተ-ትምህርት

- ተግባር ላይ ከማተኮር ይልቅ በንድፈ-ሃሳብ ላይ የታጨቀ መሆኑና ለፈተና የማዘጋጀት መርህ የሚከተል መሆኑ፣
- በሁሉም እርከን ያለው ሥርዓተ-ትምህርት አለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን መሠረት ያላደረገ፣
- በየጊዜው እየተፈተሸ የማይከለስ፤
- የአገር በቀል የዳበረ የእውቀት ክምችትን በአግባቡ ያካተተ  ተለማጭ ሥርአተ ትምህርት አለማዘጋጀት፣
- ስለቴክኖሎጂና ስለሥራ ፈጠራ በቂ ትውውቅ፣ እውቀትና ክህሎት እንዲኖራቸው አለመደረጉ፣
- ለብዝሃነት የሰጠው ቦታ እጅግ አናሳ መሆን፣

## የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ ያልቻለ የመምህራን ምልመላና ዝግጅት

ከ2006 እስከ 2009 በተካሄዱ የሙያ ፍቃድም ምዘናዎች ምዘናውን ከወሰዱት ውስጥ፤

- 140,435 የመጀመሪያ እና
- 24,063 ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ውስጥ

**የመቁረጫ ነጥቡን በማሟላት ያለፉት 22% መምህራን ብቻ ናቸው፡፡**

በ222 የገጠር፣ በ125 የከተማ በድምሩ በ347 ናሙና ት/ቤቶች በተደረገው ጥናት፤

- ወደ **12% ያህሉ** የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት መምህራን ያለምንም በቂ ምክንያት **ከት/ቤት ይቀራሉ፤**
- **28% ያህሉ በት/ቤት ውስጥ እያሉ ክፍል ውስጥ አይገቡም፤**
- **7% ያህሉ** ከዚህ በከፋ ሁኔታ **በክፍል ውስጥ ያሉ ግን የማያስተምሩ** ናቸው፡፡
- በአጠቃላይ ሲታይ በክፍል ተገኝተው በአግባቡ የሚያስተምሩት 51% ያህሉ ብቻ ናቸው፡፡

# በ2009 ዓ.ም. ለሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት ለመከታተል ፈተና የወሰዱ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ውጤት



# እጅግ አሳሳቢ የሆነ የትምህርት ቤቶች ሁኔታ

## ከ2006-2008 የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ቤቶች የኢንስፔክሽን አፈጻጸም ደረጃ



# ከ2006-2008 የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቤቶች የኢንስፔክሽን አፈጻጸም ደረጃ












BROTHER IN-LAW
SISTER IN-LAW
የ1ለ5 አደረጃጀቶች
የጥናት ቦታ


Physics
Biology























በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር

የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ጥናት

# የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና







# ችግሮችና ተግዳሮቶች

# የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ችግሮችና ተግዳሮቶች

- የተደራሽነት ችግር ያለበት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕቀፍ
- ከኢንዱስትሪው ፍላጐት ጋር ያልተሳሰረ የሙያ ደረጃ ምደባ
- ኢንዱስትሪው በእምነት ያልተቀበለው የትብብር ስልጠና እና ባለቤት ያልሆነበት የብቃት ምዘና
- የሥልጠና ጥራትን ማረጋገጥ ያልቻለ የአሠልጣኝ ምልመላና ዝግጅት
- በበቂ እውቀት ላይ ያልተመሠረተ የቴክኖሎጂ ሽግግር
- ቅንጅት የጐደለው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት
- በተለያዩ ችግሮች የተወሳሰበ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አደረጃጀትና አመራር
- በቂ ትኩረት ያልተሰጠው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የፋይናንስ ስርዓት

# ፍትሐዊነትና ተደራሽነት ያረጋገጠ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና



# የ2009 ዓ.ም. በክልል ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ብዛት




| | ትግራይ | አፋር | አማራ | አሮሚያ | ኢትዮ-ሶማሌ | ቤንሻን ጉል-ጉሙዝ | ደቡብ | ጋምቤላ | ሐረሪ | አዲስ አበባ | ድሬዳዋ | አገር አቀፍ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የወረዳ ብዛት | 52 | 35 | 182 | 333 | 83 | 21 | 168 | 14 | 9 | 117 | 13 | 1027 |
| የተቋም ብዛት | 25 | 5 | 89 | 147 | 10 | 5 | 50 | 2 | 6 | 26 | 2 | 367 |

# በ2009 ዓ.ም. ከመደበኛ ሥልጠና ውጪ በየሥልጠና ዘርፎቹ ለመመዘን ፍቃደኛ የሆኑና የተመዘኑ እንዲሁም ብቁ የሆኑ በ%



# ፖሊሲና እስትራቴጂ በተመለከተ የታዩ ችግሮች

- አሁን ያለው ፖሊስ ገዳቢ ከመሆኑ የተነሳ በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ውስጥ ጥራት ያለው መካከለኛና ከፍተኛ ባለሙያ ለማሰልጠን አለመቻል፤
- በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ምሩቃን ወደ ከፍተኛ የስልጠና ፕሮግራም እና ትምህርት የሚያሳደግና የሚያሸጋግር (Progression and Permeation) ሥርዓት መንደፍ የሚያስችል የፖሊሲ ድጋፍ አለመኖር፡- ይህ የቴክኒክና ሙያ ፕሮግራም የማያሳድግ ዝግ (Dead end) ተደርጎ እንዲቆጠር አድርጎታል፡፡
- እንዱስትሪና የግል ድርጅቶች ለቴክኒክና ሙያ ሥልጠና የራሳቸውን የገንዘብ ድጋፍ/አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የሚያበረታታ ፖሊሲ አለመኖር፤
- ከእንግሊዝኛ ሌላ ሰልጣኞች በሚችሉት ቋንቋ መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና መስጠትን የሚያስችል (Flexible Training Language) ፖሊሲ አለመኖር፤

# የቀጠለ...

- ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተደራሽነት ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የሥልጠና ተቋማትን አለማደራጀት፤
- የሀገሪቱን የኢኮኖሚ መሰረት ለሆነው ለእርሻና ግብርና ትኩረት አለመስጠት፡ - እርሻው ወይም ግብርናውን ለማዘመን እና ምርታማነት በፍጥነት ለማሳደግ የሚያስችል በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የፖሊሲ ትኩረትና የእስትራቴጂ መንደፍና መተግበር ሲኖርበት አልተሰራም።
- የተለያዩ እንዱስትሪና ኢኮኖሚ ዘርፍ ተቀናጅተው ለዘርፋቸው ተገቢ፣ ብቃትና ክህሎት ያላቸውን የመካከለኛ ደረጃ ባለሙያ ለማሰልጠን የሚያበረታታ ፖሊሲና እስትራቴጂ አለመኖር፤
- ሀገራዊ ፍላጎትን በሚገባ ያላገናዘበ የሥራ እስታንዳርድ (Occupational Standards - OS) ማዘጋጀት፤
- የትብብር ስልጠናን (Cooperative Training – Dual Training) ለመተግበር በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ እስትራቴጂ የታቀደው እቅድ ከሀገራችን ነበራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም አለመሆን፤

# የቴ/ሙ/ት/ሥ ዘርፍ የአደረጃጀት፡ አስተዳደርና አመራር

- የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ከሚመራው/ከሚያስተባብረው ባለድርሻ አካላት እና ከሚሰራው የሥራ ስፋት፣ ጥልቀትና ብዛት የሚመጥን እና ተገቢነት ያለው የፖለቲካ፡ የአስተዳደርና የአመራር ስልጣንና አቅም የሌለው መሆኑ፤
- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሥርዓት የሚመራው ተቋም፡ የሥራ ፈጠራ (የምግብ ዋስትና) እና አነስተኛና መካከለኛ እንተርፕራይዝ ማስፋፋት ኤጀንሲዎች የተሰጣቸው ኃላፊነት አቀናጅው ውጤታማ በሚሆኑት መልክ የሚመራ የበላይ የጋራ ተቋም አለመኖር፤
- የክልሎች የቴክኒክና ሙያ አስተዳደርና አመራር የአቅም ውስንነት ምክንያት ለክልሎቹ እና በውስጣቸው ላሉ ዞኖችና ወረዳዎች የኢኮኖሚ ልማት እቅዶች ጋር የሚጣጣም የሥልጠና እቅድ ማቀድና ማስፈጸም አለመቻል፤
- የሚፈለገውን የሥልጠና ደረጃ የሚመጥን ሀገራዊ የሥርዓተ-ትምህርት - ስልጠና (curriculum) እና የስልጠና መጽሐፍት (Training Materails) አለመኖር በተለያዩ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚሰጥ ስልጠና መለያየት አስተዋፅኦ ማድረጉ፤

# የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ትግበራ ጋር በተያያዘ

- ወደ ቴክኒክና ሙያ ለመካከለኛ ደረጃ ሙያ ለመሰልጠን የሚገቡ አብዛኛው ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ችሎታ ደካሞች ስለሆኑ የስልጠናው ጥራት ጉዳት እያደረሰ ይገኛል፡፡
- ጥራት (ብቃት) ያላቸው የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት እኩል ተደራሽነት ማጣት የተነሳ በተለያዩ የሀገሪቱ የሚኖሩ ዜጎች ተመጣጣኝ ብቃት ያላው ስልጠና አያገኙም፡፡
- በቴክኒክና ሙያ ስልጠና  እና በሰልጣኞች ምዘና የእንዱስትሪ ተሳትፎ ደካማ ስለሆነ ሰልጣኞች ተገቢነት ያለው የተግባርና የእንዱስትሪ ክሕሎት ምዘና ውስንነት እንዲኖረው አድርጎታል፡፡
- ከክልል ክልል ሰልጣኝ ምሩቃን የሚመዘኑበት የብቃት ምዘና ሁኔታ በጣም የተለያየ ከመሆኑ የተነሳ በተመሳሳይ የሙያ ደረጃ ብቁ የተባሉትን መወዳር አለመቻል፤

የቀጠለ . . .

- በአብዛኛው በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት የሚሰጡ የስልጠና ዓይነቶች ሀገራዊ፣ ክልላዊና ቀጠናዊ ኢኮኖሚ ከሚፈልገው የሰለጠነ የሰው ኃይል ጋር የማይናበብ መሆን፤
- ተቋማት መሀከል ያለው በመምህራኖቻቸው የሚዘጋጁ ሥርዓተ-ትምህርት/ስልጠና እና የስልጠና ማቴሪያልስ መለያየት፤
- ብቁና ተነሳሽነት የላቸው የቴክኒክና ሙያ መምህራንና አሰልጣኞች እጥረት፤
- ለቴክኒክና ሙያ ስልጠና በተማሪዎች፥ በወላጆችና እና በቀጣሪዎች ያለው ዝቅተኛ አመለካከት በተማሪዎች ጥራትና ተነሳሽነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር

የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ጥናት

# የከፍተኛ ትምህርት







# ችግሮችና ተግዳሮቶች

# ተደራሽነት

- በተደራሽነት በኩል ብዙ የሄድን ቢሆንም መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ ተደራሽነት አኳያ ገና ብዙ ይቀረናል፡፡
- ከፍትሐዊነት አንፃር ሴቶች፣ አካል ጉዳት ያለባቸው ዜጐች፣ የአርብቶ አደርና የታዳጊ ክልል ተወላጅ ተማሪዎች ተሣትፎ ዝቅተኛ በመሆኑ ብዙ መሥራት ይጠበቃል፡፡

# ብዝሃነትንና የአገር አንድነትን በተመለከተ

- እስካሁን ዩኒቨርስቲዎቻችን በብዝሃነት ሰፊ ስራ የሰሩ ቢሆንም፣ በአንድነትና በአገር ወዳድነት  ዙሪያ ምንም አልሰሩም ማለት ይቻላል፡፡

- ተማሪ ተኮር የትምህርት አሰጣጥን በትክልል አለመተግበር፣
- ያለ በቂ ሃብትና ቤተ ሙከራዎች ዩኒቨርትቲዎችን በብዛት መክፈት ፣
- አግባብነት  የሌላቸዉ የትምህርት ዘርፎችን በመክፈትና ተማሪዎችን በማስመረቅ ተማሪዎችን ለስራ አጥነት  መዳረግ ፤  ኢኮኖሚያችን ሳይፈቅድ 70/30 መከተል፣
- ተማሪዎች በተከታታይ ምዘናና በህብረት በመስራት የማይገባቸዉን ዉጤት እንዲያገኙ  ማድረግ፣
- ተማሪዎችና አስተማሪዎች  በግምገማ ለይ አለአግባብ መስማማት፣
- በተግባር የተደገፈ ትምህርት አለመስጠት ፣
- ተማሪዎች የሕይወት ዘመን ክህሎት እንዲኖራቸዉ አትኩሮ አለመስራት፣

- የትምህርን ጥራት ማስፈን የሚችል ጠንካራና ገለልተኛ የትምህርት አግባብነትና ትራት ማረጋገጫ አጀንሲ አለመኖር፣

- ጠንካራ የሆነ ጥራት ተቆጣጣሪ ባለመኖሩም የግል ዩኒቨርስቲዎች  ገንዘብ መሰብሰብ ላይ ማተኮር፣

# በ2009 ዓ.ም. ለዩኒቨርስቲ መምህርነት ተፈትነው 50% እና በላይ ውጤት




| | እንግሊዝኛ | ሒሳብ | ፊዚክስ | ኬሚስትሪ | ባዮሎጂ | ኢኮኖሚክስ | ጂኦግራፊ | ታሪክ | ማኔጅመንት | አካውንቲንግ | የተፈ.ሀብት አስ./NRM/ | የግብርና ኢኮኖሚክስ | እጽዋት ሳይንስ | የእንስሳት ሳይንስ | አጠቃላይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ድምር | 3.48 | 1.30 | 4.61 | 9.20 | 64.68 | 2.65 | 20.78 | 3.77 | 56.98 | 8.37 | 63.98 | 59.85 | 45.66 | 26.58 | 27.79 |
| ሴት | 2.86 | 0.00 | 1.45 | 2.64 | 45.19 | 0.99 | 9.74 | 1.06 | 35.94 | 1.66 | 36.50 | 40.00 | 21.29 | 11.70 | 17.67 |
| ወንድ | 3.90 | 2.17 | 6.49 | 13.45 | 80.39 | 2.84 | 25.90 | 5.26 | 62.68 | 9.53 | 74.12 | 65.42 | 55.44 | 30.41 | 31.54 |

% of Students who perform the following activities
N=228

| | |
|---|---|
| 1. Using crib notes, or cheat sheets when you give a test or an exam | 89 |
| 2. Copying from another student during a test or exam | 92 |
| 3. Copying material from any written source and turned it in as his/her own work | 89 |
| 4. Fabricating or falsifying a bibliography or reference | 74 |
| 5. Falsifying or fabricated lab data or research data | 71 |
| 6. Submitting to you a paper, at least in part, from another student’s paper | 89 |
| 7. Text messaging answers to a test or an exam to another classmate during the test or exam | 67 |
| 8. Freely accessing a ready-made assignment or term paper from the Internet | 84 |
| 9. Plagiarizing or copying and pasted an assignment from the Internet and submit as his own | 87 |

- መምህራን ለማህበረሰብ አገልግሎት ስራ  ጊዜ አለመሰጠት
- የሚጠኑ ጥናቶችም፤
  - ✓ ከሕብረተሰቡ ችግር ጋር አለመተሳሰር፣  ከመማር ማስተማሩ ጋር አለመዛመድ፣
  - ✓ አዳዲስ መምህራን የጥናትና ምርምር ክህሎት አለመኖር፣ የጥናትና ምርምር ግብአቶች አለመኖር፣ የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው።
- የሚመደበው በጀትም የዋናዉ ተልእኦ ዋነኛ ተግባራት ለሆኑት የምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት በጣም አነስተኛ ነዉ።
- አስተዳደርና አካዳሚክ ሰራተኛ ጥምርታ 3፡1 ደረጃ ይገኛል። ይህም ከአለም ስታንዳርድ ከፍ ያለ ነዉ። ብክነትን ያመለክታል።
- የተማሪዎች አገልግሎት ስራ በአብዛኛዉን ዩኒቨርስቲ አመራር ስራ ጊዜ እየወሰደ ይገኛል
- የመምህራን መኖሪያ ቤት እጥረት ወይም ደመወዛቸዉ  አነስተኛ በመሆኑ ቤት ተከራይተዉ መኖር አለመቻል፣

# የትምህርትና ሥልጠና የማሻሻያ ምክረ-ሃሳቦች

# የአጠቃላይ ትምህርት ምክረ-ሃሳቦች

# ሥርአተ-ትምህርት፤ ሥነዘዴና ምዘና

## ሀ. ሥርአተ-ትምህርት

- የትምህርትን መሰረት ለማጠንከር 0-ክፍል በአዲስ መልክ ይደራጃል፤
  - 0-ክፍል የ4-5+ ዕድሜ ያላቸዉን ህጻናት ይይዛል።
  - ሥርዓተ ትምህርቱ የህጻናትን ሁለንተናዊ ዕድገት (አካላዊ፤ አእምሮአዊ፤ ማህበራዊ፤ ስሜታዊ) በሚያመጣ መልኩ ይቀረጻል።
- ከአካባቢ ጋር እንዲቆራኝም ይደረጋል።

የቀጠለ...

# ሀ. ሥርአተ-ትምህርት

- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት **መሠረታዊ ክህሎቶችን** (ማንበብ፤ ማስላት፣ አካባቢን ማወቅና መጠበቅ፤ ወዘተ) የማዳበር ዓላማውን የበለጠ እንዲያጠናክር ይደረጋል፤
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎችን ለከፍተኛ ደረጃ ከማዘጋጀቱም በተጨማሪ ሥራ ላይ እንዲሠማሩ ያበቃል

- ስለሆነም የሙያ ትምህርት (vocational education) **በሁሉም ደረጃዎች ይከተታል።**

የቀጠለ...

## ሀ. ሥርአተ-ትምህርት...

- በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የቋንቋ፣ የሒሳብና የሣይንስ ትምህርቶችን ጥራት ማሳደግ፣
- ቴክኖሎጂ ነክ ጽንሰ -ሃሳቦችና ክህሎቶች ከቅድመ መደበኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በጥንቃቄ ማካተታቸዉን ማረጋገጥ፣
  - ቴክኖሎጂ የሚፈጥረዉንም ዕድል ለትምህርት ጥራት ማሳሳያ መጠቀም (e-learning)

የቀጠለ…

# ሀ. ሥርአተ-ትምህርት…

- ሥርዓተ ትምህርቱ አገራዊ አግባብነት ያለውና በአለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ ተወዳዳሪ ማድረግ የሚችልእንዲሆን ማድረግ፣
- ሥነጥበብ በሁሉም ደረጃዎች ትኩረት እንዲያገኝ ይደረጋል
- ሥርዓተ ትምህርቱ በተቻለ መጠን የየአካባቢዉን ፍላጐት መሠረት ያደረገ ና ተለማጭ እንዲሆን ማድረግ፣

የቀጠለ...

# ሀ. ሥርአተ-ትምህርት...

- ሥርዓተ ትምህርቱ ተማሪዎች ብዙሃነትን የሚያከብር አንድነት እንዲያጐለብቱ የሚያግዝ እንዲሆን ማድረግ፣
  - የታሪክ፣ የጂኦግራፊ፣ የተግባቦት፣ ወዘተ. ትምህርቶችን ለዚህ ዓላማ መጠቀም፣
  - በዋናነት ግን ሁሉም መምህር የሥነዜጋና ሥነምግባር መምህር እንዲሆን ማብቃት

የቀጠለ...

## ለ. የመማር-ማስተማር አካባቢና ሥነዘዴ

- አሃዳዊ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ እንደገና እንዲታይ
  - ዘዴዉ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት ቢሆንም አሁን ባለንበት ሁኔታ የሚሠራ አይደለም
- በሕፃናት መካከል ያሉትን ልዩነቶች (ልዩ ተሰጥኦ፣ ክህሎት፣ ወዘተ.) የሚያስተናግድ የመማር ሁኔታ መፍጠርና የማስተማር ዘዴን መጠቀም፣
- የትምህርት ሥነዘዴን ከመማር ዉጤት ጋር (learning outcomes) ማቆራኘት

የቀጠለ...

# ለ. የመማር-ማስተማር አካባቢና ሥነዘዴ...

- ትምህርት ከክፍል በተጨማሪ በመስክ እና በተግባር እንዲካሄድ ማድረግ
  - አሳታፊና ችግር ፈቺነትን የሚያበረታታ ማድረግ
- በቅድመ መደበኛ ደረጃ ጨዋታ ዋንኛዉ ዘዴ አድርጎ መጠቀም፣
  - ህጻናትን ያማከለ፤ እናቅስቃሴ የሚያደፋፍር

የቀጠለ...

## ሐ. ምዘናና ፈተና

- ተማሪዎች አስፈላጊውን የመማር ውጤት *(minimum learning competencies)* አምጥተው ትምህርታቸውን ማጠናቀቃቸውን ማረጋገጥ፣
  - ምዘና እውቀትን ብቻ ሳይሆን ክህሎትን፣ አመለካከትን፣ እምቅ አቅምን እንዲመዘን ማድረግ፣
    - ለዚህም ስኬት ከወረቀት ፈተናዎች በተጨማሪ የምልከታ ክህሎትን፤ ነገሮችን ተንትኖ የማቅረብ ብቃትን፤ በፕሮጀክትና በጽሑፍ ሥራዎች አማካይነት መመዘን፣
- የክፍል ምዘና ተከታታይ እንዲሆን ማድረግ፣

የቀጠለ...

# ሐ. ምዘናና ፈተና...

- ክልላዊና አገር አቀፍ ፈተናዎች የብቃት ምዘና (competence test) ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ፣
  - ክልላዊ ፈተና 6ኛ ክፍል መጨረሻ
  - አገር አቀፍ ፈተናዎች 8ኛ እና 12ኛ ክፍሎች መጨረሻ
- አገራችን በአለም አቀፍ ደረጃ ያለችበትን ሁኔታ ለመገምገም የአለም አቀፍ ምዘና አባል በመሆን መሳተፍ፣

የቀጠለ...

# መ. ተያያዥ ጉዳዮች

- የቅድመ - መደበኛ ትምህርት፣ የመጀመሪያ ደረጃና የመካከለኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የነጻና ግዴታ ትምህርት (0-G8)እንዲሆን ማድረግ፣
  - የገቢ አቅማቸው ዝቅተኛ ከሆኑ ቤተሰቦች ለሚመጡ የቅድመ መደበኛና የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች የድጋፍ ሥርአት መፍጠር (ምሳሌ፡ ምግብና የመማሪያ ቁሳቁስ)፣

የቀጠለ...

# መ. ተያያዥ ጉዳዮች...

- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን የዝቅተኛውን መካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ መሸከም በሚችል መልኩ ማስፋፋት፣
- ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ የአካዳሚክና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፎች ተለይተዉ እንዲሰጡ ማድረግ፣
- የጐልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት በፌድራል እና በክልሎች ራሱን በቻለ አደረጃጀት ተዋቅሮ እንዲሰራ ማድረግ፣

# የመምህራን ሥልጠናና ልማት

## የእጩ መምህራን ምልመላ

- በዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ምደባ ወቅት የመምህርነትን ሙያ እንደ አንድ የሥልጠና መስክ (BAND) እንዲካተት ማድረግ፣
- በኮሌጆች የኮታ አሠራርን ማስወገድ/በኮታ ለሚመጡ የተለየ ድጋፍ መስጠት፣
  - የአስፈጻሚ አካላት ጣልቃ ገብነት ይቆማል
- የመምህራን አሠልጣኞችን ለመለየት፣ ለማዘጋጀትና ለማልማት የሚያስችል፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ለሁሉም ተቋማትና እጩዎች ገዢ የሆነ የመመልመያ መስፈርት ማዘጋጀት
  - የመምህራን አሠልጣኞች በጥናትና ምርምር የሚሳተፉበትን ሥርዓት መዘርጋት

የቀጠለ...

## የእጩ መምህራን ምልመላ...

- እጩ መምህራንን 12ኛ ክፍልን የተሻለ ውጤት ካመጡት ውስጥ መምረጥ፣
  - ለሙያዉ ፍላጎትና አክብሮት እንዳላቸዉም ማረጋገጥ
- አሠልጣኝ ተቋማት በምልመላ ወቅት ቀጥተኛና ጠንካራ ተሳትፎ እንዲኖራቸዉ ማድረግ፤

የቀጠለ...

# የአጩ መምህራን ሥልጠና

- በሁሉም ደረጃዎች የእጩ መምህራንን ሥልጠና ጥራት ማሻሻል
  - የመምህራን ትምህርት ሥርአተ ትምህርት እጩ መምህራን ከምረቃ በኋላ ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር እንዲጣጣም ማድረግ፣
  - የመምህራን ሥልጠናና የትምህርት መስጫ ቋንቋ እንዲጣጣም ማድረግ፣

የቀጠለ...

# የእጩ መምህራን ሥልጠና...

- ብቁና በቂ መምህራንን ለማዘጋጀት የሚያስችሉ **የተለያዩ አማራጮችን** መጠቀም፣
  - የተጣመረውን (concurrent)፣
  - ከመጀመሪያ ድግሪ ቀጥሎ የሚሰጥ የሙያ ሥልጠና (consecutive)፣ እና
  - ሌሎችንም

የቀጠለ...

# የሥልጠና አካባቢና ሥነዘዴ፣

- በኮሌጆች ያለዉን የሥልጠና አካባቢ ምቹ ማድረግ
  - የተማሪ ማደሪያ ለሁሉም ማዘጋጀት
  - የመማሪያ ክፍሎች በቂና ጽዱ እንዲሆኑ ማድረግ
  - ላይብረሪ፤ ላቦራቶሪ፤ ኣይቲ፣ ወዘተ ማጠናከር

የቀጠለ...

# የሥልጠና አካባቢና ሥነዘዴ፤

- ለመስክና ተግባር ተኮር ዘዴ የተለየ ትኩረት መስጠት
- መሠረታዊ ክህሎት፣ የሕይወት ክህሎት እንዲሁም ከፍተኛ የአስተሳሰብ ክህሎትን በተመጣጠነ መልኩ ማስተማር፣
- የቅድመ መደበኛ መምህራንን ዝግጅት በተለየ መልኩ ማከናወን (ለምሳሌ፤ ለጨዋታ ልዩ ትኩረት መስጠት)

የቀጠለ...

# መሠረታዊ የሥልጠና ደረጃዎች፣

- ለቅድመ - መደበኛና ለመጀመሪያ ደረጃ በ12+3 ደረጃ ያሰለጠኑ፣
- ለዝቅተኛ ሁለተኛ/ከፍተኛ መጀመሪያ ደረጃ (7-10)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው፣
- ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ (11-12) ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው፣
- የትኩረት ነጥብ፤

በያንዳንዱ ደረጃ የሚመደቡ መምህራን በዚያዉ ደረጃ እስከ ሦስተኛ ዲግሪ መማር ይችላሉ።

የቀጠለ…

# ምደባና ዝውውር

- በሁሉም ደረጃ የመምህራን ምደባ ግልጽና ፍትሐዊ እንዲሆን ማድርግ
  - ብዙሃነትን በሚያጐለብት መልኩ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ምደባ ማካሄድ፣
- የትኩረት ነጥብ፡
  - መምህራን በአንድ ቦታ ረዘም ያለ ጊዜ መቆየት ብዙ ጥቅም ስላለው  እንዲቆዩ የተለያዩ አበረታች ስልቶችን መጠቀም፤

የቀጠለ...

# ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ

- ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ኘሮግራምን በትምህርት ቤትም ሆነ በኮሌጆች ተቋማዊ ማድረግ፣
  - ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ኘሮግራም በመምህራን ፍላጎት የሚወሰን ሆኖ የትምህርት አይነት እውቀትና የማስተማር ዘዴ ዝግጁነት ክፍተቶችን እንዲሞላ ተድርጎ እንደገና ማሻሻል፣
  - የሙያ ማሻሻያ ኘሮግራም ከደረጃ እድገት ጋር እና ከሙያ ፍቃድና እድሳት ጋር ማስተሳሰር፣
  - ለዚህም የሚሆን የመምህራን የብቃት ማዕቀፍ (Teachers' Qualification Framework) ይዘጋጃል፤

የቀጠለ...

# ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ....

- የክረምት የትምህርት ዋንኛ ዓላማ ደረጃ ማሳደግ ሳይሆን ሙያ ማሻሻል እንዲሆን ማድረግ፣
  - እንደአማራጭ የማታ ትምህርት፤ ሙሉ ስኮላርሺፕ፤ ወዘተ መጠቀም
  - ሌላዉ አማራጭ የቆይታ ጊዜ ማራዘም
- ደረጃ ያሻሻሉ መምህራን በዚያዉ ደረጃ ጥቅማጥቅማቸዉ ተጠብቆ የሚቆዩበት ሥርዓት መዘርጋት
  - በዚያዉ ደረጃ እስከ ሦስተኛ ዲግሪ የሚሠሩበትን ሁኔታ መፍጠር፤

የቀጠለ...

## ፈ. ጥቅማጥቅሞችና የማትጊያ ዘዴዎች፣

- የመምህራን ደመወዝ ቢያንስ ቢያንስ ከሌሎች ሙያዎች ጋር ተመጣጣኝ/ተወዳዳሪ እንዲሆን ማድረግ፣
- በጥናት ላይ ተመሥርቶ ጥቅማጥቅሞች ማሻሻል፣

የቀጠለ...

# ልሕቀት ማዕከላት ማቋቋም

- በየክልሉ ቢያንስ አንድ፣ የቅድመ-መደበኛና የመጀመሪያ ደረጃ የመምህራን ትምህርት የልሕቀት ማእከል ማደራጀት፣
- በሁለተኛ ደረጃ መምህራን ትምህርት ላይ የሚሠሩ በሚገባ የተደራጁ የልህቀት ማእከላት ማደራጀት፤
- በመምህራን ትምህርት ላይ ትኩረት አድርገዉ የሚሰሩ የትምህርት ዩኒቨርስቲዎች ማቋቋም፣
- አንድ አገር አቀፍ የመምህራ ትምህርት ምርምር እና የስትራቴጂ ኢንስቲትዩት መመሥረት፣

የቀጠለ...

# ሁሉ -አቀፍ የመምህራን ፖሊሲ ማዘጋጀት

- የመምህራንና የመምህራን አሠልጣኞችን፡
  - ምልመላ፣
  - መረጣ፣
  - የሥራ ላይ ሥልጠና፣
  - እውቅና የመስጠት፣
  - ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ፣
  - የሙያ ፍቃድ፣
  - ዝውውር፣
  - አገልግሎትን የማቋረጥ ፣ ወዘተ . ያካተተ መሆን ይጠበቅበታል፣

- የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ማካተት፤
- የመምህራን ሰርቪስ ኮሚሽን ማቋቋም

የቀጠለ...

# የመምህርነትን ሙያ ገጽታ መገንባት

- አሁን ያለዉ የተዛባ እይታ በመሠረቱ እንዲቀየር ማድረግ፡፡ እንዴት?
  - እስካሁን የተዘረዘሩ የለዉጥ ሀሳቦች ተግባር ላይ በማዋል
  - የሙያዎችን ምንነትና ጠቀሜታ ለተማሪ ወላጆች ማስገንዘብ
  - የመንግሥት ሃላፊዎችና ተዋቂ ሰዎች ስለመምህርነት ሙያ ጠቀሜታ ተከታታይነት ያለዉ ምሥክርነት እንዲሰጡ ማድረግ
  - የላቀ አስተዋጽዖ ያበረከቱ መምህራንን በከፍተኛ ደረጃ ዕውቅና መስጠት
  - በትምህርት ቤቶች ክበባት መመሥርት (ምሳሌ፤ የነገው መምህር) ወዘተ...

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር

የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ጥናት

# የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና







# ምክረ-ሃሳቦች

# ከፓሊሲ ጋር የተያያዙ የተለዩ የለውጥ ምክረ ሃሣቦች_

- ዝቅተኛ የቴክኒክ ባለሙያ፣ ቴክኒሻን ፣ ቴክኖሎጂስትና የቴክኒክ መሃንዲስ ወዘተ. ለማፍራት የሚችል የቴ/ሙ/ት/ሥ ሥርዓት መዘርጋት፤

- በሙያ ደረጃ ዝግጅትና ባለቤት ሊሆን የሚችል ሙያ መሰረት ያደረገ የተደራጀ የቴክኒሻን፣ ቴክኖሎጂስትና የቴክኒክ መሃንዲስ እና ሌሎች የዕደጥበብ ባለሙያዎች ማህበራት/ቻምበር/ ለመፍጠር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፤

- የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ስልጠና ለመሳተፍ የሚያስችል እና ወደ ከፍተኛ የአካዳሚክ ትምህርት መግባት የሚያስችል መንገድ /pathway/ መቅረፅ፤

# የቀጠለ . . .

- ዜጎች በራሳቸው ፍጥነትና ሚመርጡት የትምህርት ዘዴ እና ዝንባሌአቸውን መሠረት ባደረገ እንዲማሩ የሚደግፍ ፖሊሲ ማውጣት፤

- የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ውጤታማ ለማድረግ በተለያዩ የስልጠና ቋንቋዎች ለማሰልጠን የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፤

- እንዱስትሪና የግል ድርጅቶች በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ሂደት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የሚያበረታታ ሥርዓት መዘርጋት፤

# ስትራቴጂ ጋር የተሳሰሩ ለውጦች ምክረ ሀሳቦች

- ለሃገርና ለእያንዳንዱ ክልል ብሎም አካባቢ የሚስማማ ከባባዊ የኢኮኖሚ መሰረትና የተፈጥሮ ሀብት ግምት ውስጥ ያስገባ የስልጠና ዓይነት ማደራጀትና የትብብር ስልጠና ሥርዓት መዘርጋት፤
- በህብረተሰቡና በተጠቃሚው ስለቴክኒክና ሙያ ያለውን የተሳሳተ አመለካከት ለመቀየር የሚያስችልና የዘርፉን ገፅታ ሊገነባ የሚያችል ስትራቴጂ መቅረፅና መተግበር፤
- በሁሉም አካባቢዎች ለሁሉም ዜጐች ፍትሃዊ ተደራሽነትን በሚያረጋግጥ መልኩ አግባብነት ያለውና ጥራቱን የጠበቀ የቴ/ሙ/ት/ሥ ስትራቴጂ መዘርጋት፤
- የኢንዱስትሪዎችና የዘርፍ ባለሙያዎች ሙሉ ተሳትፎ የተረጋገጠበት የሙያ ደረጃ ማዘጋጀትና አሁን ያለውን ሙያ ደረጃ መከለስ፤

## የቀጠለ . . .

- በተለያየ የትምህርት እርከን (ከቅድመ መደበኛ ትምህርት እርከን በመጀመር) የአካዳሚክና የተግባር /ቴክኒክ/ ምጣኔ ግምት ውስጥ ያስገባ ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል እስትራቴጂና አሰራር ማዘጋጀት፤
- ተግባር ተኮር ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል የተለያዩ የኢንዱስትሪና የተግባር ልምድ ግምት ውስጥ ያስገባ የስልጠና ሞዴል መከተል (ለምሳሌ፡- አፓረንቲስሽፕ፣ የመማሪያ ፋብሪካ . . . )፤
- የስልጠና መሠረተ ልማት እጥረትና የበቁ አሰልጣኞች እጥረት ላይ ያለው ክፍተት ለመሙላት የተቀናጀ የወርክሾፖችና የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፣
- ብቁ እና ልምድ ያላቸው አሰልጣኞች ለመሳብ፣ ለመመልመልና ለማልማት የሚያስችል ስትራቴጂ ማዘጋጀት፤

# በአደረጃጀትና አመራር ጋር የተያያዙ ለውጦች ምክረ ሀሳቦች፡-

- ተገቢ፣ ብቁ እና አቅም ያለው መደበኛ፣ መደበኛ ያልሆነ እና ኢ-መደበኛ ቴ/ሙ/ት/ሥ እና የተግባረ እድ ልማት የሚያስተዳድርና የሚመራ ተቋም በሚንስቴር ደረጃ ማቋቋም፤

- በሃገር ፣ በክልል ፣ በዞን ፣ ወረዳ እና በከተማ ደረጃ ጠንካራና ውጤታማ የቴክኒክና ሙያ አደረጃጀትና አመራር መፍጠር፤

- አለም አቀፍ ተሞክሮ መሠረት በማድረግ የባለሙያዎች አለምአቀፍ ተወዳዳሪነት ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የባለሙያዎች የብቃት መመዘኛ ማዕከል /COC/ ማደራጀት፤

- ለሁሉም ለአጭርና መካከለኛ የቴክኒክና ሙያ የስልጠና እርከኖች ሥርዓተ ትምህርትና የስልጠና መጻሕፍት የሚያዘጋጅ ሃገራዊ ማዕከል ማደራጀት፤

# የቀጠለ . . .

- የፖሊሲ ሃሳብ የሚያመነጭና የየወቅቱን ሁኔታዎች በማጥናት የፖሊሲ ሃሳቦች ለመንግሥት የሚያቀርብ የቴ/ሙ/ት/ሥ/ ምርምር ተቋም ማቋቋም፤

- በቴክኒክና ሙያ ተቋማት እንዲደጋገፉ የክላስተር አደረጃጀት መፍጠር፤

- የሙያ ስታንዳርድ፣ የሙያ ስልጠና ሥርዓተ-ሥልጠና እና የክህሎት ምዘና ዘዴ (assessment instruments) የሚያዘጋጅ ብሔራዊ የየዘርፉ የሙያ ምክር ቤት (National Sector Skill Councils) ማቋቋም፤

# ከስልጠና አቅርቦት ጋር የተያያዙ

## የስልጠና ተቋማት በተመለከተ

- መደበኛ የቴ/ሙ/ት/ሥ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (በደረጃ 1 እና 2) እና በድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትና ሥልጠና (ደረጃ 3 እና ከዚያ በላይ) የሚያሰለጥኑ ተቋማት አድርጎ ማደራጀት፤
- መደበኛ ያልሆነውን የቴ/ሙ/ት/ሥ እና የክህሎት ሥልጠና ፕሮግራም በመሠረታዊ የቴ/ሙ/ት/ሥ ማዕከላት እና በልዩ ሁኔታ በተደራጁ የቴ/ሙ/ት/ሥ ተቋማት ለመሰረታዊ ክህሎትና ልዩ ልዩ መካከለኛ የእንዱስትሪ ሙያተኞች (ከደረጃ 1 – 5)፤ ማሰልጠን በሚያስችል መልኩ ማደራጀት
- ከፍተኛ ቴክኒሻኖች፣ ቴክኒካል መሐንዲሶችና ማስተር ቴክኖሎጂስቶች የሚያሰለጥኑ ከፍተኛ ቴ/ሙ/ት/ሥ ዩንቨርስቲዎች ማቋቋም፤
- በቀጠናውና በዓለም የሙያተኛ ገበያ ተወዳድረው መቀጠር የሚችሉ ወጣቶችን የሚያሰለጥኑ ተቀማት ማቋቋም፤

የቀጠለ. . .

## የስልጠና ቁሰቁስ በተመለከተ

- የቴ/ሙ/ት/ሥ ተቀማት ብቁ የሰው ሃይል ለማፍራት የሚያስችል ቁሳቁስ፣ አሰልጣኞች እና አመራር እንዲማሉ ማድረግ፤

- የቴክኒክና ሙያ ተመራቂዎች ሥራ ፈጣሪ ሆነው ሊወጡ የሚያስችል የኢንተርፕራይዞች መፈልፈያ ማዕከል /Incubation center/ ማደራጀት

- የቴክኒክና ሙያ ሰልጣኞች በአካባቢያቸው የተግባር ልምምድ ለማድረግ የሚያስችል ኢንዱስትሪ በሌለበት ሁኔታ በማሠልጠኛ ተቋም ውስጥ የመማሪያ ፋብሪካ /learning factory/ ማደራጀት፤

የቀጠለ. . .

## አሰልጣኞችን በተመለከተ

- ብቁና የኢንዱስትሪ ክህሎት ያላቸው አሰልጣኞችን ለመሳብ የሚያስችል የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት፤
- በተመረጡ የቴ/ሙ/ት/ሥ ኮሌጆችና እና የቴ/ሙ/ት/ሥ - ቴክኒካል ዩንቨርቨርስቲዎች የቴክኒክና ሙያ መምህራን ማሰልጠን እንዲችሉ ማደራጀት፤

## የብቃት ምዘና በተመለከተ

- የሙያ ማህበራት፤ የግሉ ዘርፍና የንግድ ምክር ቤቶች የሙያ ምዘና እስታንዳርድ መመዘኛ መሳርያ ዝግጅትና በምዘና እንዲሳተፉ ማድረግ፤
- ሰለጣኞች የውጤት አሰጣጥ ሥርዓት "የበቃ" "ያልበቃ" ከማለት በቁጥር የሚገለፅ ውጤት (grade) መስጠት፤

# ከገፅታ ከመገንባት አንፃር የተሰጡ ምክረ ሀሳቦች፡-

- የቴ/ሙ/ት/ሥ አቅም (ጥቅም፡ ሥፋትና ጥልቀት) በፖሊሲ አመንጪዎች፡ በአስፈጻሚዎች፡ በማሕበረሰቡ፡ በወላጆችና በተማሪዎች ዘንድ የሚያስተዋውቅ ብሔራዊ/ሀገራዊ ፕሮግራም (promotion program) መፍጠር፤

- በመካከለኛ እና በከፍተኛ ሙያ እርከን ማለትም በሰለጠነ ሰራተኛነት፣ ቴክኒሻን ፣ ቴክኖሎጂስት፡ ወዘተ ማሰልጠን የሚችሉ ምርጥ እና ለስልጠና አመቺ ድባብ መፍጠር የሚችል የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት (brand residential separate TVET institutions) መገንባት፤

# የቀጠለ.....

- የሰልጣኞች አቅምና ውጤት መሠረት ያደረገ የተለያየ የቅበላ መመዘኛና የስልጠና ሥርዓት በመዘርጋት ተወዳዳሪ ሰልጣኞች መሳብና ማሰልጠን እንዲቻል፡ - ሁሉምን ስልጠኝ በጀማሪ ሰልጣኝ (በደረጃ 1 ስልጠና) ከመቀበል ይልቅ እንደ ትምህርት ደረጃቸው ለሚመጥናቸውን የስልጠና እርከን መቀበል፤

- ተማሪዎች ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸው ጀምሮ የቴክኒክና ሙያ እውቀትና ፍላጐት እንዲያድርባቸው በሥርዓተ-ትምህርቱ የቴክኒክ/vocational/ ይዘት ባካተተ መልኩ መቅረፅ፤

- በሁለተኛና በድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ደረጃ መስጠት በሚያስችል ሁኔታ መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ስልጠናን ማደራጀት፣

- ለቴ/ሙ/ት/ሥ ሁለተኛ ደረጃ ምሩቃን ለደረጃቸው የሚመጠን የክህሎት ሰርተፍኬት እንዲያገኙ ማድረግ፤

# የቴ/ሙ/ት/ሥ ዘርፍ በፋይናንስ ማጠናከር

- ፌዴራልና የክልል መንግስታት ቴክኒክና ሙያ ፋይናንስ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት /ፎርሙላ/ ማዘጋጀት፤
- አለም አቀፍ የልማት አጋሮችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቴክኒክና ሙያ በፋይናንስ ለማጠናከር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፤
- እንዱስትሪዎችና የቢዝነስ ተቋማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉበት የስልጠና ፈንድ ማቋቋም፤
- የቴክኒክና ሙያ ተቋማት በራሳቸው አቅም የፋይናንስ ገቢያቸው የሚያሳድጉበት ሥርዓት መዘርጋት፤
- ለቴክኒክና ሙያ ተቋማት አፈፃፀም/ብቃት/ መሠረት ያደረገ የፋይናንስ ማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ጥናት

# የከፍተኛ ትምህርት





# ምክረ-ሃሳቦች

- የትምህርትን ተደራሽነት ለማሳደግ ጥራቱን በጠበቀ መልኩ non-dormitory modalities of increasing access
  - Online ና የርቀት  ትምህርት በስፋት መስጠት እንዲሁም የጥራት ቁጥጥሩን ማጥበቅ
  - ከፍተኛ ቁጥጥር በማድረግ የግል ዩኒቨረስቲዎች  ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ትምህርት እንዲያስፋፉ ማድረግ
  - ዩኒቨርሲቲዎች ሴቶችና ልዩ ፍላጐት ያላቸውን ተማሪዎች ማገዝ እንዲችሉ በበጀት መደገፍ

- የትምህርትን ተደራሽነት ለማሳደግ ጥራቱን በጠበቀ መልኩ non-dormitory modalities of ተማሪዎች በአገራችን አንድነት ዙሪያ ጥሩ አመለካከት እንዲኖራቸዉ፣ ስርአተ ትምህረቱን በተለያየ አክቲቪቲ መደገፍ
  - የአንደኛ አመት ተማሪዎችን የጂኦግራፊና አንትሮፖሎጂ ኮርሶችን መስጠት
  - በዩኒቨርሲቲዎች ዉስጥ ያሉ የጥራት ማረጋገጫ  ቢሮዎችን አወቃቀር ማስተካከል

# የቀጠለ...

- የትምህርትን ጥራት ማስፈን የሚችል ጠንካራ ገለልተኛ የሆነ የትምህርት አግባብነትና ጥራት ማረጋገጫ ኤጀንሲ እንዲኖር ማድረግ ፡ ተጠሪነቱንም ለጠ/ሚኒስቴር ወይም ለፓርላማ ማድረግ
- ያለ በቂ ሃብትና ቤተ ሙከራዎች ዩኒቨርሲቲዎችን በብዛት መክፈት ማቆም/መከልከል
- አግባብነት  የሌላቸዉ የትምህርት ዘርፎች እንዳይከፈቱ ማድረግ
- ጠንካራ የቁጥጥር ስርአት ማዘጋጀት፡
- ተማሪዎች በተከታታይ ምዘናና በህብረት በመስራት የማይገባቸዉን ዉጤት እንዳያገኙ ማድረግ
- ግምግማን በተመለከት በተማሪዎችና በአስተማሪዎች መሃከል ያለዉ አግባብ ያልሆነ ስምምነት ማስወገድ

# የቀጠለ...

- የመዉጫ ፈተና በሁሉም የትምህርት መስኮች እንዲሰጥ ማድረግ፡፡
- በተግባር የተደገፈ ትምህርት መስጠት ያሰችል ዘንድ -
  - internship 2.5 months per year for 4 years (2, 2, 3, 3)
  - ከእንዱስትሪ የመጡ ባለሞያዎች ወደ ዩኒቨርስቲ መጥተዉ እንዲያሰተምሩ ማድረግ (visiting industry professor)
- ኢኮኖሚያችን ሳይፈቅድ 70/30 ን አለመከተል (flexibly assign students)
- የሰዉ ሃይል ገበያ አንፎርሜሽን ሲስተም እንዲዘጋጅ ማድረግ፡፡ **L**abor **M**arket **I**nformation **S**ystem
- መምህራን ለማህበረሰብ አገልግሎት ስራ ቢያንስ 15% የሚሆነዉን ጊዜ እንዲሰጡ በህግ መደንገግ
-

# የቀጠለ...

- የዩኒቨርስቲ ስልጠና ከጽንሰ ሀሳብ በተጨማሪ በተግባርና በሕይወት ዘመን ክህሎት ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል።
- ተማሪ ተኮር የማስተማር ስርአትን በትክክል በተግበር
- ት/ሚ ዩኒቨረስቲዎችን ሲገመግም የግብአትን አጠቃቀም ብቻ ሳይሆን ዉጤትን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል (the MoE shall introduce university ranking system based on key performance outcome indicators)
- ዩኒቨርስቲዎች የተለያየ አደረጃጀት ተዘጋጅቶላቸዉ እንዲሰሩ ማድረግ፡ research universities, teaching universities, applied universities and technical universities
- የቅድመ ምረቃ ትምህርት ከ3 አመት ወደ 4 አመት መቀየር፤ አንተርንሽፕን ጨምሮ 5 አመት

# የቀጠለ...

- ለምርምር ስራ ትኩረት መስጠት እንዲቻል
  - ቤተ ሙከራዎች እንዲስፋፋ ማድረግ
  - መምህራን በስፋት በምርምር ስራ ኢንዲሳተፉ በጀት መመደብ (>5 %)፣ የምርምር ገንዘብን ለመጠቀም ማነቆ የሆኑትን ማስወገ ድ
- የዩኒቨርስቲ እንዱስትሪ ትስስሩ ተጠናክሮ የዩኒቨርስቲዎች የቴክኖሎጂ ሽግግርና በፓተንቲግ አጥብቀዉ ሊስሩ ይገባል፡፡
- የዩኒቨርስቲዎች የተማሪዉን ፈጠራ ስራ ለማበረታታት ኢንኩቤሽን ማእከላትንና ሳይንስ ፓርክ ማቋቋም ይኖርባቸዋል፡፡
- የዩኒቨርስቲዎች በአገር ችግር ላይ መስራት ቢኖርባቸዉም፣ የምርምር ዩኒቨርስቲዎች አለማቀፋዊንት ይዘት እንዲኖራቸው መደረግ አለበት፡፡
- ለዚህም ተጽእኖ ፈጣሪ በሆኑ በአለም አቀፍ መጽሄቶች እንዲያሳትሙ ማስገደድ፤ አገር በቀል መጽሄቶችን ማስፋፋት፤ ብቃታቸዉን ማሳደግ፣

# የቀጠለ...

- አሁን ያለዉን የግዥ ስርአት መለወጥና  የግዥ ስርኣቱ ለምርምር አመቺ እንዲሆን ማድረግ፣

- የአስተዳደርና አካዳሚክ ሰራተኛ ጥምርታ 3፡1  ወደ 1፡3 መቀየር፣ ለዚህም የተማሪዎች አገልግሎት ስራ ከዩኒቨርስቲ ዉጭ ራሱን ችሎ በካምፓኒ እንዲተዳደርና የዩኒቨርስቲ አመራር ስራወን በምርምርና አካዳሚክ ፖሊሲ ዙሪ ብቻ ቢሰራ ፣

# የቀጠለ...

- ጥቅል የበጀት ስርአትን ማሰፈን ና  የዉስጥ ገቢ አጠቃቀም ለይ ለዩኒቨርስቲዎች ሙሉ ነጻነትን መስጠት (introduce block grant and allow universities to use internal revenue flexibly)፣
- የተማሪዎች ወጪ መጋራት   ከ15% ወደ 30% ና ከዚያ በላይ ማሳደግ በምትኩ ለመክፈል አቅም የሌላቸዉ ለድሃ ተማሪዎች ነፃ የትምህርት ዕድል መስጠት፣
- ከፍትኛ የትምርት ዘርፍ ዩኒቨርስቲዎችን በብቃት ማስተዳደር (regulate ማድረግ) ይችል ዘንድ አደረጃጀቱን የተሟላ ማድረግ፣
- ቢቻል ከፍትኛ ትምህርት ዘርፍ ራሱን ችሎ በሚኒስትር ደረጃ ቢዋቀር፣

# የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ፣ አመራርና አስተዳደር

# የትምህርት ፍልስፍና

- በራሳቸው የሚተማመኑ፣ ብቁና በምክንያታዊ ትንተናና በውይይት የሚያምኑ፣ በሙያቸው ብቃት ያላቸው በአለም አቀፍ ተወዳዳሪና ብቁ ዜጋ አድርጎ አጠቃላይ ሰብእናቸውን የመገንባት፣
- ሥራ ፈጣሪዎች፣ አዳዲስ ግኝቶችን አፍላቂዎች፣ ጠንካራ የሥነ ምግባርና ግብረገባዊ እሴቶችን የተላበሱ እና ለሕግ ዘብ የቆሙ ዜጎችን የማፍራት፣
- ብዝሃነትን ላካተተው አገራዊ አንድነትና ሠላም ዘብ እንዲቆሙ የማድረግ፣
- ሕዝባዊ እሴቶች፣ ነፃነት፣ ብቃት፣ (ተጠያቅነትን፣ ጥራትንና ደረጃን ውጤታማነትን)፣ ፍትሐዊነትና ልቀትን የሚያጎናጽፍ፣

# የትምህርት መዋቅር

- ቅድመ-መደበኛ ትምህርት ሕፃናት ከ4+ - 5+ እድሜያቸው እንዲማሩ ማድረግ፣ O-class የ መደበኛ አጠቃላይ ትምህርት አካል ማድረግ።
- መደበኛ አጠቃላይ ትምህርት: 6-2-4: የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት 6+ አመት ከ1ኛ- 6ኛ ክፍል ፣
- ዝቅተኛ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከ7ኛ - 8ኛ ክፍል፣
- ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከ9ኛ – 12ኛ ክፍል (academic and TVET tracks) ፣
- ሁሉም ፕሮፍሽናል ስልጠናዎች ከ12ኛ ክፍል ከተጠናቀቀ በኋላ የሚሠጡ ይሆናሉ፥ (ድህረ ሁለተኛ ደረጃ፥ የመምህራንና የተክኒክና ሙያ)
- ከየአርከኑ ለሚያቋርጡ መደበኛ ባልሆነ ፕሮግራም የቴክኒክና ሙያ ስልጠናዎች በተለያየ ደረጃ መስጠት፣

# የቀጠለ

- መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በሰርተፍኬት ደረጃ (ደረጃ 1-2) ሲሆን፤ በኮሌጆች ውስጥ በከፍተኛ ሰርተፍኬትና ዲፕሎማ ደረጃ (ደረጃ 3-4)፤ ፖሊቴክኒኮች በከፍተኛ ዲፕሎማ (ደረጃ 5) እንዲሁም በቴክኒካል ዩኒቨርስቲዎች በመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪዎች

- የዩኒቨርስቲ ትምህርት ቆይታ 4 አመት እንዲሆን (ለኢንጂነሪንግ 5፤ ለሜዲሲን 6)፣ 2 አመት Masters, 4 አመት PhD,

# የትምህርትና ሥልጠና ቋንቋ

- ተማሪዎች በትምህርትና ሥልጠና ወቅት እውቀትና ክህሎትን በሚገባ እንዲጨብጡ ለማድረግ የሚያስችል **ተለማጭ የትምህርትና ስልጠና መስጫ ቋንቋ ፖሊሲ** ማስተዋወቅ፣
- ሶስት የአገር ውስጥ ቋንቋዎችን የመማር ፖሊሲን ማጠናከር፣
- የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ ሁለተኛ ቋንቋ ለአገራዊ የጋራ መግባባቢያና ሌላ አማራጭ ቋንቋ በክልል መካከል ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች፣ እንዲሁም ሦስተኛ ቋንቋ ለአለም አቀፍ መግባቢያ የያዘ የቋንቋ ፖሊሲ ማስተዋወቅ፣
- እንግሊዝኛ ቋንቋን ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ማስተማር፣
- ለመምህራን ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች  የስልጠና ቋንቋ  ለሚሰለጥኑለት የትምህርት እርከን ጋር የተጣጣመ ማድረግ፡
- እጩ መምህራን የተለያዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን እንዲማሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣

# የትምህርት ፋይናንስ

## የትምህርት ወጪዎች የክልሎችና የፌድራል በ2016/17

| Subsectors | Proportion out of the total sector expenditure |
|---|---|
| Primary Education (PE) | 30.7% |
| Secondary Education (SE) | 6.3% |
| Technical Vocational Education Training (TVET) | 6.7% |
| Higher Education (HE) | 48.1% |
| Others | 8.2% |

## የቀጠለ..

- የትምህርት ታክስን በጥናት ላይ ተመሥርቶ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ከከፍተኛ ትምህርት ተመርቀው የሚወጡ ተመራቂዎች ይከፍሉት የነበረው 15% ክፍያ በጥናት ላይ ተመሥርቶ እንዲሻሻል ማድረግ፣
- የትምህርት ፋይናንሱ ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ፣
- የትምህርት ፋይናንስ ያልተማከለና የትምህርት ተቋማት አውቶኖሚ ከተጠያቂነት ጋር ማስፈን፣
- ድፈረንሻል ብሎክ ግራንትን መተግበር፣ ፈንዲንግ ፎርሙላ (input based funding, performance based funding, endowment, and tuition fees) ሥራ ላይ ማዋል፡
- ለትምህርት የገንዘብ ብድር ሥርአት (Loan and Voucher System) መዘርጋት፣
- የትምህርት ወጪ አመዳደብ የታችኛዉን የትምህርት እርከን : የጎልማሶችና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትን ትኩረት የሚሰጥ፤ ከፍትህዊነትና ሊደገፉ ከሚገቡና ከወጪ አንጻር ማየት፡

የቀጠለ..

- የመንግሥት የትምህርት ወጪ ምደባ ተወዳዳሪነትንና ውጤታማነትን የሚያበረታታ እንዲሆን ማድረግ፣
- የግል ተቋማት፣ መያድ፣ ትርፍ ላይ ያልተመሰረቱ ሌሎች የውጭ ድርጅቶች በትምህርትና ሥልጠና ማስፋፋት እንዲሳተፉ ማድረግ፣
- ተጠቃሚዎች መክፈል የሚችሉት ወጪአቸዉን እንዲችሉ፡ ለታችኛዉ የትምህርት እርከን በነጻ እንዲማሩ፡ በማህበረሰብ ፋይናንስና በትምህርት ፈላጊዎች ፋይናንስ መሸፈን፡

## የቀጠለ..

- የትምህርት ተቋማት በነጻነት የውስጥ ገቢ እንዲያመነጩና እንዲጠቀሙ የሚደግፍ መመሪያ ማውጣት

- ሀገራዊ ፍሬምዎርክ ለግዢና ለበጀት አጠቃቀም ማዘጋጀት፣

- ሀገራዊ የህግ ማእቀፍ ቢዝነስና እንዱስትሪዉ ለሚፈልጉት የሰዉ ሃይል ስልጠና እንዲደግፉ የሚያበረታታ ማዘጋጀት፣

- የመንግስትና የግል ፐርትነርሺፕ ፣ በትምህርት ተቋማትና በእንዱስትሪዉ መካከል ትስስር ስርዓት መዘርጋት

# የትምህርት አደረጃጀት

- የትምህርት ሚኒስቴርን፣ የክልል ትምህርት ቢሮን፣ የዞን ትምህርት መምሪያን፣ የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤትን እንዲሁም የትምህርት ቤቶችን ሚና፣ ኃላፊነት፣ ተጠያቂነት እና ግንኙነት እንደገና ግልጽ ማድረግ፣

- የትምህርት ሚኒስቴርን ወቅቱ የሚጠይቀውን አገሪቱ በመለስተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ የምትፈልገውን የሰው ሀብት ልማት መገምባት በሚያስችል እንዲሁም ለዚህ ተልእኮ መልሰ ሊሰጥ በሚችል መልኩ ማደራጀት፣

- የጐልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት በፌድራል እና በክልሎች ራሱን በቻለ አደረጃጀት ተዋቅሮ እንዲሰራ ማድረግ፣

## የቀጠለ……

- የአጠቃላይ ትምህርትና ሥልጠናን፣ የቅድመ መደበኛ፣ የመጀመሪያ ደረጃ የመምህራንና የትምህርት አመራሩን ሥልጠና ጨምሮ ኃላፊነቱን ለክልል ትምህርት ቢሮዎች መስጠት፣

- የቅድመ-መደበኛ ትምህርት እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ወረዳ ት/ጽ/ቤት፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የዞን ትምህርት መምሪያ በኃላፊነት እንዲሠሩ ማድረግ፣

- ዩኒቨርስቲዎች እንደተልኳቸው ትኩረት ማደራጀት፤ የምርምር፣ አኘላይድ ሳይንስ፣ ቴክኒካል ዩኒቨርስቲ ሆነው እንዲደራጁ ማድረግ፣

## የቀጠለ......

- የወላጆችንና የማህበረሰቡን ተሳትፎ ለማሳደግ እንዲቻል ይህን ሥራ የሚያስተባብር አካል በወረዳ ደረጃ (ወረዳ ት/ጽ/ቤት ) ማደራጀት፣
- ነጻ የኳዋሊቲ አሹራንስ አጀነሲ ለከፍተኛ ትምህርት፤ ለመምህራን ትምህርት ፣ ለ የአጠቃላይ ትምህርትና ለተክኒክና ሙያ በሀገር  አቀፍና በክልል ደረጃ ማቋቋም፣
- የትምህርት ቤት አደረጃጀት  በተገቢ መዋቅርና የሰዉ ሃይል ድጋፍ ሰጪን ጨምሮ ማደራጀት፣

# የትምህርት አስተዳደርና አመራር

- ፖሊሲ አውጪዎችንም ሆነ በተግባር የተሠማሩትን ባለሙያዎች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አመራሮችን ልማት ለማሳደግ የሚያስችል ሥርአት መዘርጋት፣
- የትምህርት አመራሮችንና አስተዳደሮችን በተዘጋጀ ተጨባጭ መመዘኛ መሠረት ብቃት ላይ የተመሠረተና ግልጽነት ያለው ውድድር በማካሄድ መረጣ፣ ምልመላና ምደባ መካሄዱን ማረጋገጥ፣
- በሁሉም የትምህርት እርከኖች ብቃት ያላቸውን የትምህርት ቤት አመራሮችን መመደብ፣
- በሁሉም እርከኖች ዴሞክራሲያዊ የሆነ ሙያዊ አመራር ብቃትን ያማከለ እንዲሆን ማድረግ፣
- የትምህርት አመራሮችንና አስተዳደሮችን ማበረታቻን መሠረት ያደረገ በሙያ ማሻሻያ ኘሮግራም አቅማቸውን ከፍ ማድረግ፣

## የቀጠለ..

- የትምህርትና ሥልጠና ኘሮግራሞች ከአገሪቱ የኢኮኖሚ ፍላጐት ጋር መተሳሰሩን ለማረጋገጥ እንዲቻል የክልልና የወረዳ የትምህርትና ሥልጠና መምሪያዎች/ጽ/ቤቶችን አቅም ማጐልበትና ማጠናከር፣
- ልምድ ያላቸው መምህራንን ወደ ትምህርት ቤት አመራርነት እንዲያድጉ በሚያስችል መልኩ የመምህራንን የደረጃ እድገት ማዘጋጀት፤
- የሙያ ማረጋገጫ መንገዶችን  ከአመራር ስልጠናና ዝግጅት ፤ ከትምህርት ከምርምርና  ፖለሲ ጋር ማያያዝ
- በምርምር  ላይ የተሞረኮዘ ፤ራሱን የቻለ የከፍተኛ የትምህርት ተቋም ለአመራርና ለመምህራን ትምህርትና ስልጠና ማደራጀት፤
- በሁሉም እርከኖች ያሉ ተማሪዎች መሠረታዊ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል የተማሪዎችን ዳራና  አጠቃላይ መረጃ  ማደራጀት፣

## የቀጠለ..

- ትምህርት ተቋማት አግባብነት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር (ምሳሌ፣ የዩኒቨርስቲ-ኢንዱስትሪ፣ የት/ቤትመምህራን፣ ወዘተ.) ጠንካራ ትስስር መፍጠር፣
- ትምህርት ቤቶች ለአካባቢውና ለተማሪዎች ምላሽ ሰጪ እንዲሆኑ የት/ቤት ባለድርሻ አካላትን (ር/መምህራን፣ መምህራን፣ ወላጆች፣ ማህበረሰቡ) አቅም ማጠናከር፣
- የት/ቤት ወላጅ ተሣትፎን ማጠናከር፤ ወላጆች በተወካዮቻቸው አማካኝነት የልጆቻቸውን የትምህርት ውጤታቸው ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፣ ስለልጆቻቸው አጠቃላይ ደህንነት ክትትል እንዲያደርጉ ማበረታታ ያስፈልጋል።

የቀጠለ..

- እንደ መምህራን ማህበር ያሉ የሙያ ማህበራት የበለጠ ሙያዊ እንዲሆኑና በራሳቸው ሙሉ ነፃነት ኖሯቸው እንዲሠሩ አቅማቸውን ማጠናከር

- የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ነጻና ራስን በራስ የማስተዳደር ከተጠያቂነት ጋር በተቆራኘ መልኩ ማስፈን፣

- ትምህርት ቤቶች የለውጥ ማእከል፤ ያልተማከለ ውሳኔ ሰጪ፤ ባለሙያዎችን፣ ደንበኞ  ችንና ሌሎችንም በውሳኔ የሚያሳትፉ፣ በራስ የመማርን የሚያበረታቱ፣ ፈጠራን የሚደግፉ እንዲሆኑ ትምህርት ቤት ተኮር አስተዳደርን መተግበር

# የትምህርት ሕግና ፖሊሲ ማእቀፎች

- አገራዊ የትምህርት ሕግ ማዘጋጀት፣
- የቅድመ-መደበኛ ትምህርት፣ የመጀመሪያ ደረጃና የዝቅተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የግዴታ ትምህርት እንዲሆን ማድረግ፣
- በሕፃናት መካከል ያሉትን ልዩነቶችን (ልዩ ተሰጥኦ፣ ክህሎት፣ ወዘተ. ያላቸውን ሕፃናት) የሚያስተናግድ የመማር ሁኔታ እንዲሁም ልዩነቶችን የሚያስተናግድ የማስተማር ዘዴን የሚያበረታታ ፖሊሲ ማዘጋጀት፣

# የትምህርት ሕግና ፖሊሲ ማእቀፎች

- ለመደበኛ ኘሮግራም ብቃትን መሠረት ያደረገና ከቅድመ-መደበኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ የሙያ ክህሎቶችን ያካተት፣ ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ የአካዳሚክና  የቴክኒክና ሙያ  ትምህርትና ሥልጠና ዘርፎች (የሁለተኛ ደረጃ የአካዳሚክ ትምህርት ዘርፍ እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ) እንዲሁም በአካባቢ ደረጃ የአካባቢን ፍላጐት መሠረት ያደረገ ተለማጭ አገር አቀፍ የሥርዓተ-ትምህርት ፖሊሲ ማዘጋጀት፣

- የጐልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት መዋቅሩን፣ ሥርዓተ-ትምህርቱን፣ የኘሮግራሙን ተሣታፊዎችን፣ አመቻቾችን፣ በጀትን፣ የተለያዩ ሀብቶችን፣ ባለድርሻ አካላትን፣ ወዘተ. ያካተተና በሁሉም ደረጃ ባሉ የትምህርት መዋቅሮች እንዴት ማስተዳደር እንደሚቻል አቅጣጫ የሚያሳይ ፖሊሲ ማዘጋጀት፣

## የቀጠለ...

- የትምህርትና ስልጠና  ቋንቋ ፖሊሲ ተለማጭ፥ የተማሪዎችን ፍልሰት ብዘሃነትን ዓለም አቀፋዊነትን በሚያጠናክር ማዘጋጀት፥
- የትምህርትና ስልጠና ፋይናንስ  ፖሊሲ የመንግስት ትኩረትና የበጀት አመዳደብ ስርዓት ብቃትና ዉጤታማነት፥ የግልና አጋር ድርጅቶች ድርሻ ገላጭ ፖሊሲ ማዘጋጀት፥
- ራሱን የቻለ የትምህርት ጥራትና አግባብነት የሚቆጣጠር ተቋም በማቋቋም ሁሉንም የትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን እንዲቆጣጠርና የትምህርትና ሥልጠና ጥራትና እግባብነት እንዲያረጋግጥ ማድረግ፣
- በፖሊሲ አውጪዎች፣ በትምህርትና ሥልጠና አቅራቢዎች፣ በተጠቃሚዎች መካከል ጠንካራ የተጠያቂነት ግንኙነት ሥርአት መፍጠር፣

## የቀጠለ....

- የትምህርት አመራሮችንና አስተዳደሮችን ፣ የመምህራን አሠልጣኞችን ለመለየት፣ ለማዘጋጀትና ለማልማት ፣ እድገት ጥቅማጥቅሞችንና የማበረታቻ ዘዴዎች የሚያስችል ማእቀፍ ማዘጋጀት፣
- የሴት ተማሪዎችን እንዲሁም መምህራንን ምጥጥን ማሳደግ፤ የሥርዓተ-ጾታ ምጥጥኑን ለማጥበብ የሴቶችን አቅም የማጠናከርና አወንታዊ እርምጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣
- በሁሉም ደረጃዎች በመማር ውጤት ላይ ተጠያቂነትን ማስፈን፣
- በከፍተኛ ትምህርት የአስተዳደር ሠራተኞችና የአካዳሚክ ሠራተኞች ምጥጥን በ1፡2 እና 1፡3 መካከል እንዲሆን መወሰን፣

የቀጠለ..

- የአስተዳደር ሥራዎችን/በተለይ የተማሪዎች አገልግሎት  የውጪ አካል እንዲሠራው በማድረግ አመራሩ በዋና ተልእኮ ላይ እንዲያተኩር ማድረግ፣
- ከተለያዩ የትምህርት እርከኖች ፕሮግራሞች  ሽግግር ለማሳለጥ  National Qualification Framework (NQF) ሥራ ላይ ማዋል፡
- በልዩ ልዩ ደረጃዎች የሚሰጡ የሁለተኛ ደረጃ ሰርተፍኬት፣ የኮሌጅ ዲኘሎማና የዩኒቨርስቲ ዲግሪ መደበኛ የትምህርትና ሥልጠና ኘሮግራሞች ደረጃዎች በአገራዊ የሙያ ማእቀፍ ማረጋገጥ፣
- የፖሊሲ ብቃትን ማረጋገጥ፡ የፖሊሲ አፈጻጸም በፖሊሲ ግምገማ/ጥናት የማስደገፍ ስርዓት መዘርጋት

# ማጠቃለያ

- የትምህርትና ሥልጠና ሥርአታችን በበርካታ ችግሮችና ተግዳሮቶች የተሞላ ነው። ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፤
- የትምህርትና ሥልጠና ሥርአታችን በንድፈ-ሃሳብ ላይ እንጂ ተግባር፣ ክህሎትና ፈጠራ ላይ ያተኮረ አይደለም፤ የምዘና ሥርአታችንም እውቀትን ብቻ የሚመዝን ነው። ዜጎችንም በ16 አመታቸው የሁለተኛ ደረጃ እንዲያጠናቅቁ በማድረግ ከትምህርትና ሥልጠና ሥርአቱ ውጪ እያደረግናቸው ነው።
- እስካሁን እየተገበርን ያለው የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ሥራ ፈላጊ እንጂ ሥራ ፈጣሪ ትውልድ እየፈጠረልን አይደለም። በዚህ ምክንያትም ሕብረተሰቡ በትምህርትና ሥልጠና ሥርአታችን የጥራትና የተገቢነት ጥያቄ እያነሳ ይገኛል። በተለይ የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን ልጆች ከሥራ አፈናቅለን የተሻለና የሰለጠነ ትውልድ እንፈጥራለን ብለን ወደ ትምህርት ቤት አምጥተን ከተማሩ/ከሠለጠኑ በኋላ ወደ ቤተሰቦቻቸው ተመልሰው ሥራ ሲያግዙና ሥራ ሲፈጥሩ አይታዩም።

# ማጠቃለያ...

- በትምህርትና ሥልጠና የሚያልፈው ትውልድ ከትምህርትና ሥልጠናው እውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከት በበቂ ሁኔታ ይዞ ከመገኘት ይልቅ የምስክር ወረቀቱን/ዲኘሎማውን ይዞ መገኘትና ዲኘሎማ አምላኪ ሆኗል፤ በሂደቱም የኩረጃና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ጐልቶ ይታያል፡፡
- በትምህርትና ሥልጠና ያሉት ሁሉም ዘርፎችና ባለድርሻ አካላት ተቀናጅቶና ተናቦ አይሰሩም፡፡
- የምርምርና የቴክኖሎጂ ሥራችንም ጐልብቶ ኢኮኖሚው በሚፈለገው መጠን እያገዘ አይደለም፡፡
- ከሌሎች አገራት ጋር ሲነፃፀር የትምህርትና ሥልጠና ጥራታችን በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ራሳችንን የምናይበት ሥርአት አልዘረጋንም፡፡

# ማጠቃለያ...




**ስለዚህ የፍኖተ ካርታውን ግኝቶች ይዘን ከ2011 ጀምሮ ወደ ስር ነቀል ለውጥ መግባት አገራችን ከኛ የምትጠብቀው ስትራቴጂና ወቅታዊ ጉዳይ ነው።**


እመሰግናለሁ።